የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

ቀን ህዳር 4/2009

ቁጥር፡ ድ.101/2009

<u>ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የተሰጠ የስራ ሃላፊነት</u>

ይድረስ ለኢትዮጵያ አንድነት እና ነጻነት ታጋይ ወ/ሮ የኢትዮጵያወርቅ (የሐረርወርቅ)ጋሻው

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ከተመሰረተበት 1993 ዓ.ም ጀምሮ የወያኔ/ኢሃዴግን ዘረኛ ድርጅት ህዝብንና ሃገርን በመበታተንና በማጥፋት ላይ የሚገኘውን ይህን ፋሽሽታዊ ስረዓት ለመታደግ በቁርጥ ቀን የሃገር ልጆች ትግል መጀመሩ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በጅምላ ህዝብን መግደል የመረጠውን ዘረኛ ቡድን እየተፋለመ መተኪያ የሌለውን የሕይወት መስዋዕትነት እስካሁኑ ሰዓት ድረስ እየከፈለ ይገኛል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ከሚመለከታቸውና ከሚያሳስባቸው ወገኖቹ ጋር በተለያዩ ጊዜያት ፣ ከምሁራኖች ፣ከሲቪክ ማህበራት፣የተቃዋሚ -ፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም አክቲቪስት ግለሰቦች ጋር በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር እየከፈለ ያለውን መስዋዕትነትና የቆመለትን ዓላማ በማስረዳት ትግሉ የሕዝብ ድጋፍ እንዲያገኝ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ትግሉን ማጠናከር ይቻል ዘንድ በርካታ ጥናቶችንና መረጃዎችን ሲያሰባስብ ቆይቷል ።በዋንኛነት ሲደረጉ የነበሩ ውይይቶችም በዓለም አቀፍ ደረጃ የዲፕሎማሲ የሰራ ክንውኖችንና ሕዝባዊ ድጋፍን በማጠናከር በተግባር ለመተርጎም ሞያተኞችን ማዋቀር እንዳለበት በአንክሮ ያምናል።

በዚህም መሰረት ባላቸው የስነ-ሕዝብ ሞያና የስራ ልምድ *ፍጹም የሆነ ኢትዮጵያዊ ቁርጠኝነትና የትግል ተሞክሮ ወ/ሮ የሐረር ወርቅ ጋሻው በዓለም አቀ*ፍ ደረጃ የድፕሎማሲ የሰራ መምሪያ ሃላፊነት እንዲወስዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ውሳኔ ስጥቷል።

በዚህም ረገድ ወይዘሮ የሓረር ወርቅ ጋሻውም ባለዎት በዲፕሎማሲ እና የኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍ አስተባባሪነት የስራ ዘርፉን ተቀብለው ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተጣለብዎትን የዜግነት ግዴታ እና አደራ በመቀበሎዎ እያመሰገንን።

ይህንን ሃላፊነት በመቀበል የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባርን ለማጠናከር ከሚመለከታቸው የድርጅቱ መምሪያ አካላት ጋር በመመካከር አስፈላጊ የሆኑ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶችን በማድረግ ትግሉ ወደፊት እንዲራመድ በተመደቡበት መምርያ የበኩላቸውን እንዲወጡ በአክብሮት እንጠይቃለን።

አንድነት ሃይል ነው

መስከረም አታላይ (ሜ/ጀ)

የኢሕአግ ሊቀመንበር

ግልባጭ

ለኢሕአግ የተለያዩ መምሪያዎች